የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 2
ADDIS ABABA 12th December, 2006

<u>ማውጫ</u>

አዋጅ ቁጥር ፭፻፭/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በእስራኤል መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ … ገጽ ፫ሺ፬፻፹፩

**<u>CONTENTS</u>**

**Proclamation No. 505/2006**

Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Israel for the Avoidance of Double Taxation and Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation…. Page 3481

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፭/፲፱፻፺፱

## በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በእስራኤል መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በእስራኤል መንግሥታት መካከል በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችል ስምምነት እ.ኤ.አ. ጁን ፪ ቀን ፪ሺ፬ በእየሩሳሌም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በእስራኤል መንግሥታት መካከል የተደረገውን ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፭/፲፱፻፺፱” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 505/2006.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE STATE OF ISRAEL FOR THE AVOIDANCE OF DOUBLE TAXATION AND THE PREVENTION OF FISCAL EVASION WITH RESPECT TO TAXES ON INCOME

**WHEREAS,** a Convention for the Avoidance of Double Taxation and Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income (the Convention) was signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the State of Israel in Jerusalem on 2nd June, 2004;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia on its meeting held on 28th day of November, 2006 has ratified the convention;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the “Convention between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Israel for the Avoidance of Double Taxation and Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income Ratification Proclamation No. 505/2006.”

### ፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በእስራኤል መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፪ ቀን ፪ሺ፬ በእየሩሳሌም የተፈረመው በገቢ ላይ የሚከፈለውን ግብር በሚመለከት ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት እና በታክስ ላይ የሚፈፀምን ማጭበርበር ለመከላከል የሚያስችለው ስምምነት ፀድቋል።

### ፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ አግባብ ካላ ቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

### ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ ፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

### 2. Ratification of the Convention

The Convention between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Israel for the Avoidance of Double Taxation and Prevention of Fiscal Evasion with Respect to Taxes on Income signed in Jerusalem on 2nd June, 2004 is ratified.

### 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to implement the Convention in cooperation with the concerned Government organs.

### 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 12th day of December, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**